# ከፐብሊክ ሰርቪስ የሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ ዓርብ የሚታተም

PSETSE

## በድርጅቱ የቋሚ ኮሚቴው ጉብኝት

የፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት በ2005 ዓ.ም ሀምሳ አምስት ተሽከርከሪዎችን ይዞ ለአስር ሺህ ሰራተኞች አገልግሎት በመስጠት ስራ መጀመሩ ይታወሳል። ድርጅቱ ስራውን ከጀመረበት ወቅት አንስቶ ለመንግስት ሰራተኛው በስራ መግቢያና መውጫ ሰዓቶች አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ በተለይ የጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ ለሚኖሩ ሰራተኞች ከፍተኛ ግልጋሎት እየሰጡ ናቸው፡፡ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የከተማ መሰረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት የመስክ ምልከታና ውይይት አካሂዷል፡፡ የቋሚ ኮሚቴውን የመስክ ጉብኝት በተመለከተ ከፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅትና ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማህበራዊ ድረገፅ ያገኘነውን መረጃ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡

ቋሚ ኮሚቴው በጠዋቱ ክፍለ ጊዜ ሠራተኛ ወደ ስራ መግቢያ ሰዓት ላይ በተለያዩ የጉዞ አቅጣጫዎች በመገኘት የመስክ ምልከታ አድርጓል፡፡ ከመስክ ጉብኝቱ በኋላ ከድርጅቱ ስራ አመራር አባላት ጋር ጥያቄና መልስ ያደረጉት የቋሚ ኮሚቴ አባላት በጉብኝታቸው ወቅት የተመለከቱትን ጥንካሬና መስተካከል ይገባቸዋል ያሏቸውን ሐሳቦች አንስተው ምላሽ የተሰጣቸው ሲሆን፣ የድርጅቱ የስራ አመራር አባላት ከቋሚ ኮሚቴው አባላት የተነሱና ሊስተካከሉ የሚገቡ አስተያየቶች በግብአትነት ወስደዋል፡፡



ድርጅቱ በተለያዩ ዘርፎች እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ ለሌሎች ተቋማትም እንደ ተሞክሮ ሊወሰድ እንደሚገባ የጠቀሰው ቋሚ ኮሚቴው፤ በተለይ ድርጅቱን እንደ ራዕዩ ሁሉ ቀልጣፋና ተደራሽ ለማድረግ የበለጠ የተጠናከረ ስራ ሊሰራ እንደሚገባ አመላክቷል፡፡ ቋሚ ኮሚቴው የፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት በየጊዜው የሚያሻቅበውን የሰራተኛ ቁጥር ታሳቢ በማድረግ መስራት እንዳለበት አስገንዝቧል። ድርጅቱ ተገልጋይ የመንግሥት ሰራተኞችን ቁጥር ለይቶ ያለመያዝ ጉድለቱን በማስተካከል በየጊዜው እያሻቀበ የሚገኘውን የሰራተኛ ቁጥር ታሳቢ ያደረገ አገልግሎት ለመስጠት አቅዶ መስራት እንዳለበት ጠቁሟል፡፡

የትራንስፖርት አገልግሎቱን በተሟላ መልኩ ለመስጠት እንዲቻል ከአዲስ አበባ አስተዳደርና ከአንበሳ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት ጋር ያለውን ቅንጅት ማጠናከር እንደሚገባ ያስታወሰው ቋሚ ኮሚቴው፤ ተቋሙ አልፎ አልፎ የሚታየውን የአሽከርካሪዎች ስነ-ምግባር ጉድለት እንዲሁም ፎርማታን የመዝለል መሰል ጉድለቶችን መመልከት እንዳለበትና የተጀመሩ መልካም አፈጻጸሞችን አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚገባ ተናግሯል።

ቋሚ ኮሚቴው የድርጅቱን ዋና ጽህፈት ቤት የጎበኘ ሲሆን፣ የድርጅቱ ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ፍሬህይወት ትልቁ፤ የድርጅት አገልግሎት አሰጣጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻሎችን እያሳየ መምጣቱን እና እያንዳንዱን የተሽከርካሪና አሽከርካሪ እንቅስቃሴ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመቆጣጠር አገልግሎቱን ምቹና ቀልጣፋ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን ያብራራሉ፡፡

ዋና ዳይሬክተሯ፤ ተቋሙ በቀጣይም ከፐብሊክ ሰርቪስ አገልግሎት ባሻገር ለታክሲ አገልግሎት የሚሆን ዘመናዊ የካርድ አከፋፈል ስርዓትን በመጠቀም ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ጅምር ስራዎች እየሰራ መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡ ነገር ግን የተሟላ አገልግሎት ለመስጠት በየጊዜው ከሚያድገው የሰራተኛ ፍሰት ጋር ተያይዞ ተጨማሪ የተሽከርካሪ ግዥ መፈጸም እንደሚያስፈልግም ያስረዳሉ፡፡

‹‹ሁሌም የቋሚ ኮሚቴው አባላት ለድርጅታችን የሚሰጡት አስተያየትና የስራ መመሪያ ለድርጅታችን ስኬት መሠረት ነው፡፡›› ያሉት ዋና ዳይሬክተሯ፤ ከቋሚ ኮሚቴው አባላት የተሰጡትን የጥንካሬ ማበረታቻዎች የራስ በመሆናቸው በክፍተትነት የተጠቆሙትን ለይቶ በመስራት ለበለጠ ውጤት እንደሚሰራ ያመለክታሉ፡፡

ተቋሙ በቅርቡ የተሰጠውን የተሽከርካሪ ታርጋ የማምረት ኃላፊነት በተመለከተ በተገልጋይ ዘንድ ቅሬታ እያስነሳ ስለመሆኑም ተጠይቆ ድርጅቱ የምርት ዕጥረትም ሆነ ጉድለት እንደሌለና በርካታ ታርጋዎች ተመርተው በማከማቻ መኖራቸውን ለቋሚ ኮሚቴው አሳይቷል፡፡ በተቋሙ የስምሪት ኃላፊ አቶ አማኑኤል ተዘራ በበኩላቸው፤ ለቅሬታው ዋና ምንጭ የሆነው ከዚህ በፊት በዱቤ ሲሰጥ የነበረውን አሁን ላይ ድርጅቱ ያለ ቅድመ ክፍያ የማይሰጥ መሆኑ ነው ሲሉ ለቋሚ ኮሚቴው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

### በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት

አቶ ሚካሊ ማኖሊ የተባሉ ግለሰብ የተሽከርካሪው ዓይነት ባጃጅ የሞተር ቁጥር 3009173 የሆነ ኮድ 1-17642 ደህ ሰሌዳ ጠፋብኝ በማለት በ17/03/2014 ዓ.ም. በመሆኑም ሰሌዳውን ወድቆ ፣ ተሰርቆ ያገኘ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ወይም በሌላ ጉዳይ ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ህጋዊ ማስረጃ ይዞ ይቅረብ፡፡ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ/ የቤንች ሸኮ ዞን ትራ/መንገድ ልማት መምሪያ**

### ኦሮሚያ ክልል

ንብረትነቱ በአቶ ኢፋንዲ ኢብራሂም ስም የተመዘገበ የሰሌዳ ቁጥር 1-18611 ኦሮ የሆነ ተሽከርካሪ የፊት ሰሌዳ የጠፋባቸው መሆኑን በመግለጽ በምትኩ ሰሌዳ እንዲሰጣቸው ጠይቀውናል፡፡ ስለሆነም ሰሌዳውን ወድቆ ፣ ተሰርቆ ያገኘ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ወይም በሌላ ጉዳይ ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ - ህጋዊ ማስረጃ ይዞ ይቅረብ፡፡ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**የምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ትራንስፖርት ባለሥልጣን**

ንብረትነቱ በሰይድ አብደላ ስም የተመዘገበ የሰሌዳ ቁጥር 3-57169 የሆነ ተሽከርካሪ ታርጋ የጠፋባቸው መሆኑን በመግለጽ በምትኩ ሌላ ሰሌዳ እንዲሰጣቸው ጠይቀውናል፡፡ ስለሆነም ሰሌዳው ወድቆ፣ተሰርቆ ያገኘ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ወይም በሌላ ጉዳይ ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ህጋዊ ማስረጃ ይዞ ይቅረብ፡፡ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የጅማ ከተማ ትራንስፖርት ባለሥልጣን**

የባለንብረቱ ስም አረጋኸኝ ከበደ የተሽከርካሪ ዓይነት ሞተር ሳይክል የሰሌዳ ቁጥር 02-9215 ኦሮ የሻንሲ ቁጥር MD634KE69E2151517 ሞዴል ትሸስ የሞተር ቁጥር OE61C 2179104 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር 02-9215 ኦሮ ጠፋብን ብለው በ1/3/2014 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡ የሰሌዳ ቁጥር 02-9215 ኦሮ ወድቆ፣ተሰርቆ ያገኘ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ወይም በሌላ ጉዳይ ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ህጋዊ ማስረጃ ይዞ ይቅረብ፡፡ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን።

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የዱከም ከተማ አስተ/ትራንስፖርት ባለሥልጣን**

### አዲስ አበባ አስተዳደር

በይግባኝ ባይ -አቶ ሄኖክ ፍቅሩ በመልስ ሰጪ -እነ ወ/ሪት ሳባ ተክሉ መካከል ባለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ 2ኛ መልስ ሰጪ ዶ/ር ጀሚላ ከድር ለጥር 20 ቀን 2014 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት 1ኛ ፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

አመልካች፡- ወ/ሮ እየሩሳሌም ቴዎድሮስ ተከሳሽ፡- አቶ ኢሳያስ ቡልቡላ መካከል ስላለው ቤተሰብ ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ 2ኛ ቤተሰብ እየታየ መሆን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሁፍ በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡ እና ክስ ለመስማት ለ30/05/2014 ዓ.ም 3፡30 ሰዓት እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

ከሳሽ/ አመልካች ወ/ሮ ሱአድ አህመድ መሀመድ በከሳሽ/ተጠሪ አቶ ካሊድ ሀሰን መሀመድ መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ ቤተሰብ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ ተጠሪ በ24/05/2014 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

ከሳሽ/አመልካች፡- ቢ ጂ አይ ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህ በተከሳሽ/ተጠሪ፡- ቡፌ ዳ ላጋሐር ኃ/የተ/የግ/ማህ መካከል የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 7ኛ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ ተጠሪ በ24/05/2014 ዓ.ም ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ስላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

ከሳሽ :- ፓን አፍሪካ ግሎባል ኃ/የተ/የግ/ማ ተከሳሽ :1. አቶ ዜና ብርሀኑ 2. ማሪያ ኮንስትራክሽን ዕቃ አቅራቢ መካከለኛ በፍታብሔር ስላለው ክስ ጉዳይ ተከሳሽ በ23/5/2014 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ለመ/ደ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ 10ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

ከሳሽ/አመልካች፡- ወ/ሮ አትክልት ይኑር አህመድ በተከሳሽ/ተጠሪ፡ - አቶ ረመዳን ሀሰን መሀመድ መካከል የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ ቤተሰብ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ተጠሪ በ17/05/2014 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡45 ሰዓት ስላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

ይግባኝ ባይ አቶ አማከለው ነገደ ፍቅሬ እና መ/ሰጭ ወ/ሪት ኤልሻዳይ ዮናስ አማኑኤል መካከል ባለው የፍታብሔር ጉዳይ ወ/ሪት ኤልሻዳይ አማኑኤል በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግላቸው ፍ/ቤቱ በ3/5/2014 ዓ.ም. በዋለው ችሎት አዟል፡፡ በዚህ መሠረት መ/ሰጭ የሆኑት 1. ወ/ሪት ኤልሻዳይ ዮናስ አማኑኤል በ1/06/2014 ዓ.ም. በ4፡00 ሰዓት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ 6ኛ ፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት ድረስ እንድትቀርቡ አዟል፡፡ በቀጠሮ ቀን የማይቀርቡ ከሆነ ግን ጉዳዩ በሌሉበት የሚታይ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ያሳውቃል፡፡

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቦሌ ምድብ ችሎት**

የባለንብረት ስም መሀመድ አሊ የቁ.እ.የአስ.ተዋፅኦ የሸቀጦች ጅምላ ንግድ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A21106 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻሲ ቁጥር JAALP34G777P10314 ሞዴል NPr66 የሞተር ቁጥር 4HF1-505634 የሊብሬ ቁጥር 359825 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ2/5/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ዳዊት አዲስ ነጋሽ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-15261 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻሲ ቁጥር XLAAG25-450025854 ሞዴል 2500 የሞተር ቁጥር D-80243 የሊብሬ ቁጥር E0105143 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ4/5/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአራዳ ቅ/ጽ/ቤት**